# ★ዴሞክራሲያ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ዴሞ ቅጽ 42 ቁ. 6 ግንቦት/ሰኔ 2009


## የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝና ኢትዮጵያ

አፍሪቃን፥ ላቲን አሜሪካንና እስያን ተቆጣጥሮ የቆየው የቅኝ አገዛዝ፥ በርካታ የሰው ህይወትና ንብረት ያወደመው የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከተገባደደ በኋላ፥ በዓለም ላይ የተለያዩ ግንኙነቶችና ለውጦች ተከሰቱ። በሶቭየትና በአሜሪካ የሚመራ ሁለት ካምፕ ተፈጠረ። ይህም የቀዝቃዛው ጦርነት ዘመን በሚል ታውቆ እስከ 1980-ዎቹ (እአአ) መጨረሻ ድረስ ዘልቆ ታሪክ ሆኖ ለማለፍ በቃ። ኢትዮጵያ አባል ሆና የቆየችበት ሊግ ኦፍ ኔሽንስ ተብሎ ይታወቅ የነበረው ተቋም ፈርሶ የዓለም መንግሥታት ድርጅት በተባለውና እስከዛሬም በቀጠለው ተቋም ተተካ። ይህ ተቋም በውስጡ የሴኩሪቲ ካውንስል የተባለ አካል ፈጥሮ በጦርነቱ አቸናፊ ሆነው የወጡት ሃገሮች ማለትም አሜሪካ፥ ሶቭየት ህብረት (የዛሬዋ ሩሲያ)፥ ቻይና፥ እንግሊዝና ፈረንሳይ ቋሚ ኣባላት እንዲሆኑ አድርጎ ሰየመ። ጦርነቱ ያስከተለው የኢንዱስትሪ ውድመትና ሌሎች የዓለም አቀፍ የንግድና የመሳሰሉት እንቅስቃሴዎችም ከፉኛ ደቀው ነበርና በቅኝ ግዛትነት ተቀፍድደው ለቆዩ አገሮች ነፃነታቸውን ይጎናፀፉ ዘንድ መልካም አጋጣሚ ተፈጠረላቸው። ቅኝ ገዢዎች እንደቀድሞው የመበዝበዝና ትርፍ የማጋበስ ተግባራቸውም እዚሁ ዘመን ላይ እንዲያከትም ሆነ።

ይህ ክስተት የቀድሞ ቅኝ ገዥዎችን እንቅልፍ የሚነሳ ሆኖ ብቅ አለ። ብዝበዛና ትርፍ ማግበስበሱን እንደቀድሞው ማስቀጠሉ የማይቻል እንደሆነ ግንዛቤ ላይ የተደረሰ ቢሆንም ሌሎች የተለያዩ ዘዴዎችን ነድፎ ግን ይህንኑ ብዝበዛና ትርፍ የማግበስበሱን እንቅስቃሴ ማስቀጠል እንደሚቻል ድምዳሜ ላይም ተደርሷል። በዚህ ዘመን የተመሰረተው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጦርነቱ ያስከተለውን የኤኮኖሚ የፖለቲካና የማህበራዊ ቀውስ ለመቋቋም በተለይም የዓለም አቀፍ ንግድንና የገንዘብ ልውውጥን በአስችኳይ መልክ ለማስያዝ ይረዳ ዘንድ ዋና መሥሪያ ቤቱን በዋሽንግተን ዲሲ ያደረገውን የዓለም አቀፍ የገንዘብ ምንጭ፣ የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት (አይ ኤም ኤፍ)-ን ያቋቁማል። ይህ ተቋም አላማዎቼ ናቸው ብሎ ያሰፈራቸው መርሀ-ግብሮች ማለትም የዓለም አቀፍ የገንዘብ እርዳታ ትብብርን፥ ዓለም አቀፍ ንግድን፥ ከፍተኛ የሥራ መስክ መፍጠርን፥ የገንዘብ ምንዛሬ ልውውጥ የተረጋጋ እንዲሆን መቆጣጠርን፥ ያልተቋረጠ የኤኮኖሚ እድገት እንዲኖርና አባል አገሮች የፋይናንስ ችግር በገጠማቸው ወቅት እንደገና እንዲቋቋሙ ለማድረግ የሚረዳቸውን አቅርቦት ማዘጋጀትን የመሳሰሉ ይገኙባቸዋል። ከላይ እንደተገለፀው በሴኩሪቲ ካውንስል ውስጥ በቋሚነት አባል ሆነው የተሰየሙት አገሮች አውሮጳያውያኖቹ ቅኝ ገዢዎች የነበሩ ናቸው። በዚያም ዘመን ቢሆን በተለይም በጦርነቱ ወቅት ከመጀመሪያው ጀምሮ

ተሳትፎ ያልነበራቸውና ወደ መጨረሻው ላይ የተካፈሉት እንደ አሜሪካ ያሉቱ፤ የፋይናንስና የኤኮኖሚ አቅማቸው ጎላ ያለ ስለነበር የተቋሙን ሥራ ለማካሄድ የሚያስፈልገውን ወጪ አብላጫውን የሚያዋጡ በመሆናቸው በማናቸውም የድርጅቱ እንቅስቃሴዎች ላይ ጫና የማድረግ አቅሙ ያኔም ሆነ ዛሬ አላቸው። እነሆ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ከተመሰረተበት ወቅት አንስቶ  በዓለም ውስጥ ያለውን የእድገት አለመመጣጠንን፥ ድህነትን ለማስወገድ፣ …ወዘተ የሚሉ ስብሰባዎችንና ውሳኔዎችን እያደረገ ቢቆይም በዓለማችን ላይ ጎልቶ የሚታየው ግን ሃብታሞቹ አገሮች ይበልጥ እየከበሩ ታዳጊ አገሮች የተባሉቱ ደግሞ ይበልጥ እየደኸዩ መሄዳቸውን ነው። ይህ ደግሞ የሚያሳየው፤ የአዲሱ ወይም የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ የቀድሞውን ቅኝ አገዛዝ  ቁጥጥር፥ ብዝበዛውንና ትርፍ ማጋበሱን በሌላ ዘዴና መንገድ አስከብሮና አስቀጥሎ እንዳለ ያለ መሆኑን ነው።

ኢትዮጵያ በቀደሙት ጀግኖችና አርበኞች ልጆቿ ከባድ መስዋዕትነት፥ በተደጋጋሚ የተቃጣባትን የቅኝ አገዛዝ ጥቃት ድባቅ መትታ ነፃነቷንና ህልውናዋን ያስከበረች ጥቁር አፍሪካዊት አገር መሆኗን ወዳጆቿም ጠላቶቿም የተቀበሉትና በታሪክም ተገቢውን ቦታ ይዞ ተከብሮ የተመዘገበ ሐቅ ነው። ይህ የቀደሙት አያት ቅድማያት ወገኖቻችን የአርበኝነት ገድል ያስመዘገበው ታላቅ ድል፣ በዚያን ጊዜው ለዓለም የነበረው አስተጋብዖና እንደምታው እጅግ ከፍ ያለ እንደነበር የአገራችንም ሆኑ የውጭ ሃገር የታሪክ ፀሃፊዎች በተደጋጋሚ ዘግበውታል። በተለይም በአፄ ምኒልክ መሪነት በነቂስ ከዳር አስከዳር ኢትዮጵያውያን በአንድ ላይ ተምመው አድዋ ላይ የጣልያንን ፋሽስታዊ እብሪት የማስተንፈሳቸው ዜና ሲስተጋባ፥ በቅኝ ግዛት ሥር ወድቆ ማንነቱ ለተረገጠውና ነፃነቱ ለተገፈፈው አፍሪካዊ፥ በዓለም ተሰራጭቶ ለሚኖረው ጥቁር ህዝብና ሌሎች ጭቁን ህዝቦች ታላቅ የምሥራች ሆኖ ነበር። ባንጻሩ ደግሞ ለነጭ ሕዝብ በአጠቃላይ፥ በቅኝ ገዥነት ተሰማርተው ተዘግቦ የማያልቅ ግፍ ሲያደርሱ ለነበሩት ደግሞ ትልቅ ውርደትንና ሃፍረትን አከናንቦ እንደነበር ታሪክ መዝግቦታል። ይህ የኢትዮጵያውያን የጅግንነት ቀንዲል በዚያን ዘመን ከቅኝ አገዛዝ ሥር ራሳቸውን ነፃ ለማውጣት በየቦታው ትግል ሲያካሂዱ ለነበሩ አፍሪካውያንና ለሌሎች ጭቆን ሕዝቦች ያስተጋባው መልእክት እጅግ ኃያል ነበርና፥ ቅኝ አገዛዝ ማንነቱን ላደበዘዘውና ሰብዕናውን ለገፈፈው ጥቁር ሕዝብ ያበረከተው ልዩ የመንፈስ ብርታትና ተስፋ ወሰን እንደሌለው ብዙ ብዙ የተባለለት ነው።  የራስ ኃያልነትን፥ ጥናትን፥ በራስ መተማመን፥ ባንድ ላይ አብሮ መመከትን፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ ቅኝ አገዛዝን ፀንተው ከታገሉት ሊያስወግዱት እንደሚችሉ ማስመዝገቡ ብቻ ሳይሆን፥ ኢትዮጵያንም በልዩ አይን እንዲያዩዋት አድርጓል፤ በሌላው ወገን በነጩ መንደር ኢትዮጵያን ጥርስ ውስጥ ያስገባ እንደነበርና እስከዛሬም ቁጭቱና ጥላቻው እንዳለ ያለ መሆኑ ያደባባይ ምሥጢር እንደሆነ የሚያከራክር አይደለም ብለን እናስባለን።

እንደሚታወቀው ቅኝ አገዛዝ በዓለማችን ላይ ይፋ ሆኖ ብቅ ያለው በሰው ልጆች የእድገት ታሪክ ሂደት ውስጥ አስራ ዘጠኝ መቶ ምእተ ዓመት መጨረሻ አካባቢ ላይ የማምረቻ ኃይሎችን በይዞታነት ሙሉ በሙሉ የተቆጣጠሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ብቅ ባሉበትና የአምራቹን ኃይል ጉልበት በርካሽ በመበዝበዝ ትርፍን የማጋበስ እንቅስቃሴን እንደ ዋና ዓላማና ግብ አድርገው በተግባር ማዋል ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ መሆኑን የኅብረተሰብ የእድገት ታሪክ ላይ ሰፊ ጥናት ያካሄዱ ፀሃፊዎች በሰፊውና በጥልቀት ዘርዝረው አቅርበዋል። በዘመኑ በእንዱስትሪ የበለፀጉ አገሮች በወል ስማቸው አውሮጳያውያን የተባሉቱ እንደ እንግሊዝ፥ ፈረንሳይ፥ ጣልያን፥ ፖርቱጋል፥ ቤልጅም፣ …ወዘተ የየአገራቸውን አምራች ኃይላት መበዝበዙ ብቻ የትርፍ ማካበት ቋታቸውን ሙሉ በሙሉ የሚያረካ ሆኖ ስላላገኙት፤ ይህንን አባዜያቸውን ያስታግሱ ዘንድ የተቀረውን ክፍለ ዓለም

“ማቅናት” በሚል ሥም መቆጣጠሩን ብቸኛ አማራጭ ሆኖ ያገኙታል። በዚህም አፍሪካን፥ ደቡብ አሜሪካንና እስያን በቅኝ ግዛትነት ለመቆጣጠር ተንቀሳቀሱ፤ኃይላቸውንም ተገን በማድረግ የነዚህን ህዝቦች አገራዊ ነፃነት ገፈው፥ ብሄራዊ ማንነት ደፍረው፥ የቅኝ ገዥነትን መዋቅር ለመትከል በቁ። እነሆ ከሁለት መቶ ዓመታት በላይ (በአንዳንዱም ከዚያም በላይ) በነዚህ ክፍለ ዓለማት የሚኖሩትን ሕዝቦች ሰብዕናቸውን ብቻ ሳይሆን ጉልበታቸውንና አንጡራ የተፈጥሮ ጥሬ ሃብታቸውን እጅጉን በሚሰቀጥጥና መረን በለቀቀ ዝርፊያ ተሰማርተው ወደ የአገሮቻቸው በማጋዝ የኢዱስትሪዎቻቸውን ምርት የማሳደጉን እንቅስቃሴ በሰፊው ተያያዙት። የምርቱንም ውጤት ለዓለም ገበያ በማቅረብ እንዳቀዱት ሁሉ የትርፍ ትርፍ ሲያጋብሱ ቆዩ። አውሮጳውያን ቅኝ ገዢዎች ዋና ስምሪታቸው ትርፍ ማግበስበስ ነበርና ይህንን ጥማቸውን ለማርካት ያመቻቸው ዘንድ በቅኝ ግዛትነት የተቆጣጠሩዋቸውን አገራት ህዝቦች ላይ የኤኮኖሚ ብዝበዛና የተፈጥሮ ህብት ዘረፋ ብቻ ሳይሆን፥ ሰብእናቸውን፥ ማንነታቸውን፥ ባህላቸውንና ወጋቸውን ሁሉ ቀስ በቀስ በማጥቆር በማጉደፍ፤ በመሸርሸርና ብሎም ደብዛው እንዲጠፋና የቅኝ ገዢዎቹ ባህልና ወግ የበላይነቱን እንዲይዝ ለማድረግ ሳይታክቱ ሠርተዋል። የቅኝ ተገዢዎቹ ሕዝቦች ላይ ልዩ ልዩ የሰለሉ ዘዴዎችን በመጠቀም በመካከላቸው ስምምነትና መቀራረብ እንዳይኖር አድርገዋል። የቅኝ ገዥዎቹ ሰብዕና ብቻ የበላይነትና ተቀባይነት ያለውና የቅኝ ተገዥዎቹ ሕዝቦች ግን ሁልጊዜም ቢሆን በተፈጥሮአቸው አነስተኛና የበታች እንደሆኑ አምነው እራሳቸውን እንዲያዩና እንዲቀበሉም ጭምር ሆን ተብሎ ጫና ይደረግባቸው እንደነበር ታሪክ መዝግቦታል። ይህ የቅኝ አገዛዝ በተለይ በአፍሪካውያን ላይ ያደረሰው ክፍተኛ በደል እነሆ አፍሪካውያኑ ባደረጉት የነፃነት ተጋድሎ ተቸንፎ በሂደት ከሁሉም አገራት እንዲወገድ ከሆነ ወዲህና አገሮችም ፖለቲካዊ ነፃነታቸውን ካረጋገጡም በኋላ፤ ዛሬም ድረስ በሁሉም መስክ እምርታ አሳይተው ወደፊት እንዳይገሰግሱ ቅኝ አገዛዙ ተክሎ ያለፈው ድርጊት የአንበሳውን ድርሻ የሚይዘው ነው ቢባል የሚያስኬድ ይሆናል ።

ለጀግኖች ልጆቿ ምስጋናው ይድረስና፥ ኢትዮጵያ የቅኝ ግዛት ሰለባ ሳትሆን በመቅረቷ የተነሳ በማንነቷ፥ በራሷ የመተማመንና ኩራቷ ላይ እንደሌሎቹ የአፍሪቃ ወንድሞችና እህቶች በደል ሳይደርስባት ቀርቷል። በታሪክ እንደተዘገበው በዓለም ለይ ተንሰራፍቶ የቆየው የቅኝ አገዛዝ መሠረቱ ብዝበዛ ላይ ያተኮረ የኤኮኖሚ እንቅስቃሴ ማካሔድ ነበርና በዓለም ላይ እጅጉን ያልተመጣጠነ የሃብት ክፍፍል እንዲፈጠር አድርጎ ጥቂቶችን የናጠጡ ከበርቴዎች አብዛኛውን የዓለም ሕዝብ ግን በድህነት አረንቋ ውስጥ ጥሎት ሲያማቅቀው እንደኖረ ብዙ የተባለለት ነው። ያም በመሆኑ በቀጥታ በቀንበሩ ሥር ወድቀው በነበሩት ሕዝቦችና በየቅኝ ገዢዎቹ አገራት ውስጥ በሚኖሩት ጉልበት ሻጭ ሠራተኞች ጭምር በተደረገው መራራ ትግል፥ እንዲሁም የዓለም የሥልጣኔ ጎዳና ያስከተላቸው ልዩ ልዩ ለውጦች ታክለውበት፥ በሂደት ቅኝ አገዛዝን እያዳከሙት በመምጣታቸው፥ እንደቀድሞው ሊቀጥል የማይችልበት ሁኔታ ውስጥ እንዲገባ ተገደደ። የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከተገባደደ ከአሥር ዓመታት በኋላ እንዲያከትም ሆነ።

በዚህም በዓለም ላይ በቅኝ ተገዥነት ሥር ወድቀው የቆዩ አገራት በሙሉ አንድ በአንድ ብሔራዊ ነፃነታቸውን ሊጎናፀፉ ችለዋል። ዛሬ በቀድሞው ዓይነት ቅኝ አገዛዝ ቁጥጥር ሥር ያለ አንዳችም አገር የለም። እነሆ በቅኝ አገዛዝ ሥር የቆዩ አገራት ብሔራዊ ነፃነታቸውን ከተጎናፀፉ ወደ60-ዎቹ ዓመታት እየደረሱ ነው። በነዚህ በርካታ ዓመታት በተለይ በኢትዮጵያና በሌሎች የአፍሪቃ አገራት ውስጥ እድገትና ብልፅግና እውን ሆኖ እመርታ ያሳየበትና የሕዝቦች ፖለቲካዊ፥ኤኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሁኔታ ወደ ተሻለ ደረጃ የገሰገሰበት ሁኔታ ውስጥ ይገኛል ብሎ ለመናገር የሚያስደፍር አልሆነም። ከቶ ለምን?

ማለቱ ተገቢ ጥያቄ ይመስለናል። ቀደም ብለን እንዳስተዋልነው፥ የቅኝ አገዛዝ ዋና ባህሪውና ተልኮው ብዝበዛን መሰረት ያደረገ ትርፍን ማግበስበስ ነው። ይህ እንቅስቃሴውም በአንድ በተወሰነ ክልል ብቻ ሳይገደብ ድንበር ጥሶ የተጓዘና የዓለምን ሰፊ ግዛት ያካተተም ነበር። አገዛዙ ቀድሞ በሚያረገው ሁኔታ ሊቀጥል የማይችልበት ደረጃ ላይ መቃረቡን ሲያሰላና ሲገነዘብ ህልውናውን የግድ በሌላ ዘዴና መንገድ ሊያስቀጥል የሚያስችለውን ንድፈ ሃሳብ ማርቀቅ አስፈለገው። በዚህም ነፃነታቸውን በትግላቸው የተጎናፀፉት አገሮችና የቀድሞ ቅኝ ገዢዎች መካከል የነበረው የኤኮኖሚና ፖለቲካ ትስስር በሌላ መንገድ ይቀጥል ዘንድ የእጅ አዙር ወይም አዲሱ ቅኝ አገዛዝ በሥራ ላይ እንዲውል ተደረገ። ሁኔታውን ቀደም ብለው የተገነዘቡ በተለይም በቅኝ አገዛዝ ሥር ተወልደው ያደጉና የመማርና የማወቅ እድሉ ገጥሟቸው አገራቸውንና ህዝባቸውን አስተባብረው ለነፃነት ተጋድሎ ያበቁ አፍሪቃውያን ወንድሞች ውስጥ አንዱና ታዋቂው የጋናው ተወላጅ ኩዋሜ ኑኩሩማ፥ ይህን ግንኙነት እንዲህ በማለት ገልጾታል

“የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ፍሬ ነገሩ በሥሩ ያለን አገር የይስሙላ ነፃነት እንደ አንድ ብሄራዊ ህልውናውን እንዳስከበረ አገር አስመስሎ ማቅረቡ ሲሆን በተጨባጭ ግን እውነታው የሚያረጋግጠው የአገሩ የኤኮኖሚ አወቃቀርና አሠራርና የፖለቲካ ፖሊሲ የሚመራው ከውጭ መሆኑን ነው”

ከዚህ ከኑክሩማ አነጋገር የምንረዳው ቁም ነገር፤ በቅኝ ግዛትነት ሥር ቆይተው ነፃነታቸውን ለመጎናፀፍ በቅተዋል የተባሉት አገሮች አሁንም እጣ ፋንታቸውን እንዳሻቸው የሚዘውሩት እነሁ የቀድሞ ገዢዎቻቸው መሆናቸውን ነው። አዲሱ ወይም የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ የድንበር ጣሹን ዲታ ብዝበዛና የትርፍ ማጋበስ ጥሙን፣ ልዩ ልዩ ዘዴዎችን ተጠቅሞ የሚያረካበት ንድፈ ሃሳብ ነው የተባለውም በዚሁ የተነሳ እንደሆነ ግልፅ ነው። በመሰረቱ የዚህ እትም አላማ ቀደም ብሎ በታወቁ ታላላቅ ምሁራንና የታሪክ ተመራማሪዎች በሰፊውና በዝርዝር የተገለፀውን የአዲሱ ቅኝ አገዛዝ ምንነት ላይ ያተኮረ እንዳልሆነ አንባብያን እንዲያውቁት እንሻለን። ከላይ ጠቅለል ባለ መልኩ ስለ ጉዳዩ እንድናነሳ የሆነው ዛሬ አገራችንን የሚጠሉና በክፉ ዐይን የሚያዩዋት አገሮችና የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ተዋንያን፤ በአካባቢው የሚያካሂዱት እንቅስቃሴ ያለውን አንድምታና ብሎም አደጋውን ቀድመን ከወዲሁ ነቅተን ለመከታተል ይረዳን ይሆናል ከሚል የቀረበ ነው።

ኢትዮጵያ የቅኝ አገዛዝን ድባቅ መትታ ነፃነቷንና ብሔራዊ ህልውናዋን ያስከበረች ሀገር ብትሆንም አንዷ የዓለም ኅብረተ ሰብ አካል ናትና፣ የዓለምን የፋይናንስና የገንዘብ አቅምን ለመቆጣጠር ከተነሳው እንቅስቃሴ ማምለጥ ችላለች ብሎ ለመናገር እንደማይቻል እሙን ይመስለናል። ቀደም ያለውን ጊዜ እንተወውና በተለይ አሜሪካ በህዝባችን ላይ ወያኔን እንዲቆናጠጥ ካደረገች ወዲህ፤ ባለፉት ሃያ ስድስት ዓመታት በልዩ ልዩ ግንኙነት አማካኝነት የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሕዝባችንን እየጎዳ እንዳለ እንደ አዲስ የሚነገር ጉዳይ አይመስለንም። በጥቅሉ ግን ዛሬ አገሪቱ ለውጭ ኃይላት በሰፊው ወለል ብላ የተከፈተች በመሆኗ ለብዝበዛና ለትርፍ ማግበስበሱ ከመጋለጧ ባሻገር ለማህበራዊ ቀውስና ለውጭ ኃይላት ርካሽ ባህል መፈንጫ ሆና ያለች አገር ሆናለች። ዛሬ በአፍሪቃ ቀንድና በቀይ ባህር ሰላጤ ዙሪያ፣ በአሜሪካ አጋፋሪነት ለሚመራው ኃይል፤ የአውሮፓውያን የንግድ መስመር እንዳይሰናከልና አሸባሪ ኃይላት የተባሉትን እንቅስቃሴ ለመከላከል ኢትዮጵያ የያዘችው ጂኦግራፊያዊ ክልል ወሳኝነት አለው ተብሎ በመታሰቡ የተነሳ ይህንኑ ጥቅማቸውን ለማስከበር አገልግሎት እየሰጠች

ትገኛለች። እንደሚታወቀው ከሸርማርኬ ጀምሮ ሶማሊያ በአጎራባች አገሮች ውስጥ ሶማሌዎች ሰፍረው የሚገኙበትን ሥፍራ ሁሉ በይገባኛልነት ከተቀረው የሱማሌ ግዛት ጋር ለማጠቃለል በነበራት እቅድ የተነሳ ከኢትዮጵያ ጋር የዚያድ ባሬ መንግሥት እስካከተመ ድረስ በተለያየ ወቅት ጦርነት ስታደርግ የቆየች መሆኗ የታወቀ ነው። የዚያድ ባሬ መንግስት ሲፈርስ አገሪቱ መንግስት አልባ ሆና በተለያዩ የጦር አበጋዞች የእርስ በርስ ጦርነት ውስጥ እንድትታመስ ሆነ። በሂደት ከአረንቋው ውስጥ ለመውጣት ተስፋ የተጣለባቸው አንድ ላይ ተባብረው የነበሩ ኃይላትን፤ የአለቃውን የአሜሪካንን ትእዛዝ ለመፈፀም ወያኔ ይህንን የተባበረ ኃይል ወግቶ ከማስወገዱም በተጨማሪ፣ ዘምቶ የነበረው ወታደር ሴቶችን በመድፈሩ ከፉኛ የተበሳጩት ዛሬ አል ሸባብ ተብለው የሚታወቁት እንዲፈጠሩ ምክንያት ሆነ። እነሆ ወያኔም ባካባቢው የራሳቸውን ስምሪት ያደረጉ አለቆቹን (የምዕራባውያን አገራትን) ፍላጎት ለማሟላትና የሚያፈሱለትን ንዋይ ለመሰብሰብ ሲል ብቻ በተደጋጋሚ በሰው አገር ጣልቃ ገብቶ መርዷቸው እንኳ እስከ ዛሬ ለቤተሰቦቻቸው ያልተነገረላቸው ወታደሮች የጥይት ሰለባ ሆነው በየበርሃው የጅብ እራት ሆነው እስኪቀሩ ድረስ ያደረገው/የሚያረገው እንቅስቃሴ ለተባሉት ኃይላት አፍሪካውያንን የማዳከምና የመከፋፈል ተልዕኮ አስፈጻሚ መሆኑ ግልጽ ነው። ይህ የወያኔ ድርጊት በወደፊቱ የኢትዮጵያና የሶማሌ ሕዝቦች መካከል ሊኖር በሚገባው ግንኙነት ላይ ሊያስከትል የሚችለው መዘዝ የጎላ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም። ሌላው ትኩረት መስጠት የሚገባው ጉዳይ፤ ቀድሞም በከፉ ዐይን የሚያየን የአረቡ ክልል በተለይ የተባበሩት የአረብ ኢምሬቶችና ሳውዲ እንግሊዝ ምስራቃዊውን የሲውዝ ካናል በ1971 ዓም ለቃ ከወጣች ከ45 ዓመታት በኋላ ምዕራባዊውን የስዊዝ ካናልን በቁጥጥር ሥር ለማድረግ ከ1980 እስከ ዛሬ ድረስ እያደረጉት ያለው እንቅስቃሴ ክትትልን የሚሻ ነው።

ኢትዮጵያ የምእራቦቹም ሆነ የቻይና ኢምፔሪያሊዝም መፈንጫ ሆና ትገኛለች ። ወያኔን ለማስወገድ የተጀመረው ትግል የዚህን አንደምታ ይዞት በአግባብ ማጤን እንዳለበትም ግልጽ ነው ። የአፍሪካ ቀንድና የቀይ ባሕርም የአረቦችና ኢራን መራኮቻ መሆኑም ይታያል ። ሀገር አድን ትግላችን ይህንንም በዕይታው ማስገባት ይኖርባታል ማለት ነው ። በሉዓላዊነት ላይ የተቃጡትን አደጋዎች ሁሉ መቋቋም ለመጪው ትውልድ የማይለገት ግዳጅ ነውና ሁሉም ነቅቶ ለኢትዮጵያ ዘብ መቆሙ፤ የውስጥና የውጭ ጠላቶቿን መታገሉ ብሄራዊ ሀላፊነት ነው ።

ኢትዮጵያን ከእጅ አዙር እንጠብቅ!!

ሀገራችን በነፃነት ለዘላለም ትኑር!!